የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!

የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው!

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት!

የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!

ክቡራትና ክቡራን!

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116 (2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመስሪያ ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ዓመታዊ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ ይህን ሪፖርት አጭር ሪፖርት አቀርባለሁ፡፡
2. በዚህ አጭር ሪፖርት የዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2008 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ መ/ቤታችን በ2007/2008 በጀት ዓመት ያከናወነው የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና ሪፖርት በቀደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም

የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም

3. በ2008 በጀት ዓመት የተጠናከረ የኦዲት ልማት ሠራዊት ለመገንባትና የአቅም ግምባታ ስትራቴጅዎች አፈፃጸምን 70% ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ የአመለካከት ለውጥ የሚለካባቸው ጉዳዮች ከዕውቀትና ግንዛቤ አንፃር አጠቃላይ የመ/ቤታችን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ ራዕይ፣ ዕቅዶችና አጠቃላይ የህግ ማዕቀፎች መገንዘብ፣ ማወቅና በእምነት መፈጸም፣ ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የጸዳ ተቋማዊ ሁኔታ መፍጠር፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይፈጠሩ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳለጥና የሥራ ታታሪነትን መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ ስራ ነው፡፡
4. የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተለያዩ መድረኮች ተካሂደዋል፣ ከተግባርና ከተሞክሮም መማማር ተችሎአል፡፡ የመ/ቤታችን ሰራተኞች ያለባቸውን መንግስታዊ ኃላፊነትና የመድረኩን ተልዕኮ በመገንዘብ በኩል ጥሩ መሻሻል እየታየ ነው፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን ከመታገል አንፃር ተቋማዊ ሚናችን ይበልጥ ማጠናከር

የሚገባን ስለመሆኑ መግባባት የተደረሰበት ጉዳይ መሆኑና የስራ ታታሪነትን ከማጎልበት አንፃርም ለኦዲተሮች የተሻለ የስራ አካባቢ እንዲፈጠር በተደጋጋሚ ይቀርብ የነበረውን የጥቅማጥቅም ጥያቄ መመለሱ በጥንካሬ የሚጠቀሱና ለውጥ የታየባቸው አፈፃፀሞች ናቸው፡፡

5. ከዚህ በላይ የተመላከቱ የአመላካከት ለውጥና አንድነት አበረታች ውጤቶች የማምጣታቸውን ያክል ሰራዊት ግንባታው የሚጠበቅበትን ያክል ለውጥ እንዳያመጣ እንቅፋት የሆኑ የአመለካከት ችግሮችም አሉብን፡፡ የመጀመሪያው ችግር በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር እንዲሁም በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ግንዛቤ የመያዝና በዕምነት የመፈጸም ጉዳይ የሲቪል ሰርቪሱ ተልዕኮ ነው ብሎ ለተፈፃሚነቱ መትጋት ላይ አሁንም ውስንነቶች መኖራቸው፤ ይህና መሰል ተግባራት የመ/ቤቱን ሙያዊ ነፃነት የሚነካ ነው የሚል አስተሳሰብ አሁንም ውስን በሆነ ሁኔታም ቢሆን የሚራመድ መሆኑ፤ አልፎ አልፎም ቢሆን የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስትራቴጂው የስራ ሠዓትን በመሻማት ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር ነው ብሎ ማየት የሚሉት የሚስተዋሉ ውስንነቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከመንግስት ሠራተኛው ባህሪና ሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ የመንግስት የስራ ሰዓትን መሸራረፍ (ከመስክ ኦዲተሮች አንፃር ደግሞ በመደበኛ የስራ ጊዜ መጥፋት፤ የግል ስራን መስራት) ይስተዋላሉ፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት ዝንባሌዎችን አጥብቆ በመታገል በኩል ውስንነት ያለ መሆኑና የአገልግሎት አሰጣጣችንም በሚፈለገው መልኩ ቀልጣፋ፤ ፍትሐዊና ሙሉ በሙሉ ደንበኛን በሚያረካ መልኩ ከመፈፀም አንፃር የሚቀሩን በርካታ ስራዎች አሉ፡፡

6. በክህሎት የመፈፀም አቅምን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በየደረጃው ጥራት ያለውና ችግር ፈቺ ዕቅድ የማቀድ አቅም መሻሻል እያሳየ ነው፤ በዋናነት የዓላማ ፈፃሚ ባለሙያውን የክህሎት ክፍተት መሠረት ያደረገ የሥልጠና ሥርዓት በመዘርጋት የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መነሻ (ወንድ 42 ሴት 7 በድምሩ 49 ጀማሪ ኦዲተሮች፡- ከነዚህ ውስጥ ወንድ 38 ሴት 7 በድምሩ 45 ወጣቶች) የቅድመ ስራ የኦዲት ስልጠና ፕሮግራም በመቅረፅ ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን ነባር ኦዲተሩም ያለበትን የክህሎት ክፍተት የለየና በዓመት ከ40-80 ሠዓት እንዲሰጥ የሚጠበቀውን ተከታታይ ስልጠና መስጠት ተችሎአል፡፡ የባለሙያውን የትምህርት ደረጃ የሚያሻሻል ስራም ውስን በሆነ መልኩም ቢሆን ተጀምሮአል፡፡ የ1ለ5 አደረጃጀት ውይይቶች መደበኛ የሙያ ክህሎት ሽግግር የሚካሄድባቸው መድረኮች ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

ከክህሎት ስትራቴጂ አፈፃፀም አንፃር አሁንም የሚታዩ ውስንነቶች አሉ፡፡ የባለሙያው ክህሎት

በሚፈለገው መልኩ የተቀራረበ አለመሆን፣ ከስራ ላይ ስልጠና አሰጣጣችን ጋር በተያያዘ በተለይም የባለሙያውን የክህሎት ክፍተት መለየት የሚያስችል ወጥ አሰራር አለመዘርጋት፣ የስልጠናን ፋይዳ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አለመለካትና ተግባር ተኮር የመሆን አዝማሚያቸው ውስንነት ያለበት መሆን የሚሉት ናቸው፡፡

7. ከአደረጃጀት አንፃር በመ/ቤታችን የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን ጨምሮ 9 የልማት ቡድንና 69 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተጠናክረው ስራ ላይ ናቸው፡፡ አደረጃጀታችንን ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ ከማስገባት አንፃር በዚህ በጀት ዓመት አዲስ ምሩቃንን በጀማሪ ኦዲተርነት ለመቅጠር የተቀመጠውን ክልላዊ አቅጣጫ በመተግበር የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዓላማ ፈፃሚዎችን በአብዛኛውና በዋናው መ/ቤት በተወሰነ መልኩ ማሟላት ተችሎአል፡፡ ከአደረጃጀት አንፃር በውስንነት የታዩና በቀጣይ መፈታት ያለባቸው ጉዳዮች የቅ/ጽ/ቤት የፑል አገልግሎት የመ/ቤቱን የሰው ሃይልና በጀት አስተዳደር ልዩ ባህሪ ታሳቢ ያላደረገ መሆን፣ ከአደረጃጀት አንፃር ሌላው ውስንነት የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲትን ራሱን አስችሎ በማደራጀት ወደ ስራ ማስገባት አለመቻል የሚሉት ናቸው፡፡

8. አራተኛው የኦዲት ሰራዊት ግንባታ ስትራቴጂ አሰራር ነው፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ለክልል ምክር ቤት አባላት ወጥ የሆነ የአቅም ግንባታ ማንዋል በማዘጋጀት 187 ለሚሆኑ ለክልል የምክር ቤት አባለት እና 1064 ለሚሆኑ ወረዳ ምክር ቤት አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሎል፡፡ ይህም አሰራራችንን ከማሻሻል አንጻር ጥሩ ስራ የሰራንበት ነው፡፡ ከአሰራር አንፃር ሌላው የትኩረት ነጥብ ወቅታዊ የሆነ ኦዲት ተደራጊዎችን የምንለይበትና ስምሪት የምንሰጥበት ማስተር ሊስት ዝግጅት ተጠናቆ ወደ ስራ ተገብቶአል፡፡ የኦዲት አስተያየት መስጫና ጥንቅር መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ተገቢ ማጠናከሪያ ግብዓቶችን በማካተት ላይ ስንሆን የተፈቀደላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ በማሻሻል ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ለኦዲተሮች የተጠቃለለ የህግ ማዕቀፍ ፓኬጅ እንዲደርሳቸውም ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

9. ከግብዓት አንፃር በበጀት ዓመቱ በመደበኛነት በግዥ የሚከናወኑ የስራ ማስኬጃ (አላቂና ቋሚ) ግብዓቶች በዕቅድ እንዲመሩ ተደርጓል፡፡ የኦዲቱን ስታንዳርድና የባለሙያዎችን የመፈፀም አቅም ሊያግዙ የሚችሉ የተለያዩ ግብዓቶችን ማሟላት ተችሎል፡፡ ከግብዓት አንፃር ጎልቶ የሚወጣ ውስንነት ባይኖርም የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከቢሮ ጥበት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት ይጠይቃል፡፡

10. በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከዚህ በላይ የተመላከተው የአቅም ግምባታ ስትራቴጅዎች አፈፃፀም አንፃራዊ በሆነ መለኪያ ሲታይ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ ለመለካት ጥረት ተደርጓል፡፡ በጥናታዊ ዳሰሳ ለመፈተሽ እንደተሞከረው የአቅም ግምባታ ስትራቴጅዎች አፈፃፀም 60% አካባቢ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ይህም ለአመቱ በዕቅድ ተይዞ ከነበረው 70% አንፃር አፈፃፀሙ 86% ነው፡፡ በዕርግጥም ይህ የመለካት ሒደት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረ በመሆኑና የጥናቱ የራሱ ውስንነቶች እንዳሉ ሆነው ለመነሻ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም በጥንካሬና በድክመት የተገመገሙ የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎች ከዳሰሳ ጥናት ውጤቱ ጋር ተዳምረው በጥሞና ሲፈተሹ የቁልፍ ተግባሩ አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ መሻሻል ያሳየና አጠቃላይ አፈፃፀሙ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሠራዊት ቁመና ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

የውጤት ተኮር አፈፃፀምና የመልካም አስተዳደር ችግሮች አፈታት

11. የውጤት ተኮር ሥርዓት ከሪፎርም ፕሮግራሞች መካከል ትኩረት ተሰጥቶት በመተግበር ላይ ከመሆኑም ባሻገር አጠቃላይ ውጤቱም ከሌሎች ሪፎርም ስራዎች ጋር ተዳምሮ የመፈጸም አቅሙ የተሻለና መልካም አስተዳደርን ያሰፈነ ተቋማዊ ሁኔታን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይም ኦዲት በአጠቃላይ የመንግስት አሰራር ግልፀኝነትን የተላበሰና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ጎላ በመሆኑ በዚሁ አግባብ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ ውጤት ተኮር የዕቅድና የኮሚኒኬሽን መሳሪያ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ የመለኪያ ስርዓት ሆኖ የመ/ቤታችን ሰራተኞች በ2008 በጀት ዓመት በ1ኛው ግማሽ ዓመት ውጤት ከተሞላላቸው 265 መካከል (ወንድ 54 ሴት 10 በድምሩ 64 ሠራተኞች ወይም 24%) ከፍተኛ ያገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 201 (ወንድ 149 ሴት 52 ሰራተኞች ወይም 76% የሚሆኑት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ የተፈረጁ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በኩል የደረሰን ግብረ-መልስ የሚያሳየው የግሽበት አዝማሚያ በመሆኑ ለቀጣይ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ነው፡፡

12. የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዕቅድ ይዞ ከመፍታት አንፃር ጥሩ መሻሻሎች አሉ፡፡ በተደጋጋሚ ይነሱ የነበሩት የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥ ጉዳይና የመ/ቤታችን ኦዲተሮች የተለያዩ ጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ በቀጣይ አሁንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በሚል የለየናቸው የልዩ ኦዲት ጥያቄዎችን በወቅታዊነትና በጥራት ምላሽ ከመስጠት፤ የባለሙያውን ሥነ-ምግባር

ከማሻሻልና ከኦዲት ግኝቶች አጠቃላይ የማሻሻያ እርምጃች ትግበራ ጋር በተያያዘ አሁንም ውስንነት ያለባቸው ናቸው፡፡

የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች አፈፃፀም

13. ከኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራችን አንፃር የመጀመሪያው ተግባር የነበረው ለክልል፣ ለብሄረሰብ ዞንና ለወረዳ ምክር ቤት አባላት በኦዲት ምንነትና ፋይዳ ላይ ግንዛቤ መፍጠር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ለምክር ቤት አባላት የአቅም ግንባታ ሰነድ በማዘጋጀት 187 ለሚሆኑ ለክልል የምክር ቤት አባለት እና 1064 ለሚሆኑ ወረዳ ምክር ቤት አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሎል፡፡ የኦዲት አገልግሎቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳዩ የተለያዩ መረጃ የሚሰጡ ህትመቶች ታትመው ለባለድርሻ አካላት እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡ ሚዲያን በመጠቀም መረጃን ለህበረተሰቡ የማዳረስ ተግባርም በበጀት ዓመቱ ተጠናክሮ ተፈፅሞአል፡፡ የህዝብ ክንፎችን ከማሳተፍና ከመደገፍ አንፃርም መሻሻሎች አሉ፡፡

የኦዲት ሥራ ዕቅድ አፈፃፀም

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት አፈፃፀም

14. በ2008 በጀት ዓመት በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 60% ለማድረስ ታቅዶአል፡፡ ይህም ቅድሚያ ተሰጥቶ ኦዲት መደረግ ከሚገባቸው 442 መ/ቤቶች አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ሆኖም በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በፈጠርነው አቅም በ11 ወሩ 278 መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ዕቅድ ተይዞ በኦዲት መሸፈን የተቻለው የ258 መ/ቤቶችን በመሆን አፈፃፀሙ 92.8% ነው፡፡ ይህ አፈፃጸም የኦዲት ሽፋናናችንን 58.3% አድርሶታል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከ60% በላይ የኦዲት ሽፋን እንደሚኖረን ከወዲሁ መተንበይ ይቻላል፡፡

15. ከበጀት አንፃር እስከ 70% የወጪ በጀት የኦዲት ሽፋን ለማድረስ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ለክልሉ የተፈቀደው አጠቃላይ በጀት ብር 21,526,627,543 በመሆኑ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች አጠቃላይ በጀት ብር **17,130,995,857.81 የኦዲት ሽፋን ያገኙ በመሆኑ** አፈፃፀሙ 79.6% መድረሱን ማየት ይቻላል፡፡

የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አፈፃፀም

16. በበጀት ዓመቱ 12 ክዋኔ ኦዲቶችን (6 መደበኛና 6 የክትትል ኦዲቶችን) ለመፈጸም ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ የዕቅዱ የ11 ወር አፈፃፀም ሲታይ የመደበኛ ኦዲቶች አፈፃፀም ከ95% በላይ በመሆኑ የሪፖርት ጥንቅር ስራ ጎን ለጎን እየተሰራ የክትትል ኦዲት ስራ ተጀምሮአል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ዕቅድ በተያዘለት ጊዜ ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጅ በባለሙያዎች

መልቀቅ ምክንያት ሁለት የክዋኔ ኦዲቶች (የተቀናጀ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግርም 50% እንደደረሰ፣ ግብርና ቢሮ ስለተፈጥሮ ሃብት 20% እንደደረሰ) ተቋርጠዋል፡፡

የኦዲት ክትትልና የሙያ ብቃት ፈቃድ አሰጣጥ አፈፃፀም

17. የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 (2) (ሀ) መሰረት የመንግስት መ/ቤቶችንና የልማት ድርጅቶችን በውክልና ኦዲት እንደሚያስደርግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት 16 ለሚሆኑ የልማት ድርጅቶችና የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ሒሳባቸውን ኦዲት ሲያስደርጉ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ተችሎአል፡፡

18. የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ አሰጣጥን በሚመለከት የፌደራል መንግስት ለክልሎች የሰጠውን ውክልና መነሻ በማድረግ መ/ቤታችን አዲስ መመሪያ አውጥቶ ፈቃድ መስጠት የጀመረ ሲሆን በግንቦት ወር 148 የሚሆኑ አመልካቾች ፈቃድ ለመውሰድ ፈተና የተቀመጡ ሲሆን 136 ተፈታኞች ፈተናውን ያለፉ በመሆኑ ፈቃድ ወስደው ገበያውን የሚቀላቀሉ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የክልላችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና የኦዲት አገልግሎት ጥራት ሁኔታን የተመለከቱ የጥናትና ምርምር ስራዎች በበጀት ዓመቱ ተጠናቀው ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡

19. **የሰው ሃይል መዋቅር መረጃ**

ተ.ቁ ሂደቶች	ዋና መ/ቤት		ቅርንጫፍ ጽ/ቤት		ጠቅላላ ሰራተኛ	
	መዋቅር	ሽፋን	መዋቅር	ሽፋን	መዋቅር	ሽፋን
1. ኦዲት ዋና የስራ ሂደት	149	148	97	72	246	220
2. ህዝብ ግንኙነት	7	6	0	0	7	6
3. ደጋፊ የስራ ሂደቶች	61	60	14	14	75	74
ድምር	217	214	111	86	328	300

ማስገንዘቢያ፡-የሰው ሃይል መዋቅሩ ሽፋን 91.5% ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት በታሳቢ ቀጥር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ጨምሮ ወንድ 21 ሴት 13 በድምሩ 34 (ሁሉም ወጣት) ቅጥር ተፈፅሟል፡፡ የሰው ሃይሉ በፆታ ወንድ 226 ሴት 74 ድምር 300 [ከዚህ መካከል 181 (60.3%)] ወጣቶች ናቸው፡፡ በትምህርት ዝግጅት ዲግሪና ከዛ በላይ ሴት 44 ወንድ 193 ድምር 237 (79%) ናቸው፡፡

የበጀት አፈፃፀምና አጠቃቀም

20. በ2008 በጀት ዓመት በምክር ቤታችን የፀደቀና የተፈቀደው የመደበኛ በጀት ብር 28,078,963.00፣ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 1,000,000.00 በድምሩ ብር 29,078,963.00 ፀድቆ ወደ ስራ ተገብቶአል፡፡ የ11 ወሩ አፈፃፀም ሲታይ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ ብር

11,121,765.60፣ ለስራ ማስኬጃ ብር 11,535,238.31 በድምሩ ብር 22,657,003.91 በመሆኑ አፈፃፀሙ **80.6%** (ዋናው መ/ቤት 88.2% እና ቅርንጫፍ መ/ቤቱ 64.9%) ነው፡፡ በአጠቃላይ የበጀት አፈፃፀሙ ሲታይ ዝቅተኛ የሚባል ነው፡፡ ከመደበኛ በጀት አንፃር ለዝቅተኛ አፈፃፀሙ ዋናው ምክንያት የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 20% የሚሆኑት መደቦች ባለሙያዎችን ለመቅጠር ተይዞ የነበረው በጀት በሰው ሃይል ባለመያዙ ምክንያት ነው፡፡

21. የካፒታል በጀቱ በቅድመ ዝግጅት ስራዎች ማለትም የዲዛይንና ማማከር አገልግሎት ስራ የተስራ ሲሆን የጥገና ስራ አሸናፊ ድርጅት ለመለየት ሁለት ጊዜ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊ ድርጅት እስከአሁን አልተለየም፡፡
22. በበጀት ዓመቱ ከልማት አጋሮች ማለትም ከከተሞች የመሠረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP-II) ብር 6,543,154.00 እና ከመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም (PBS-III) ብር 1,578,500.00 ድጋፍ አግኝተን ነበር፡፡ አፈፃፀሙ ሲታይ ከULGDP-II ብር 3,556,588.19 የተጠቀምን ሲሆን ብር **2,575,000.00** ለመኪና ግዥ ግዴታ የተገባበት በመሆኑ በድምሩ 6,131,588.19 ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ አፈፃፀሙ 93.7% ነው፡፡ በሌላ በኩል የPBS-III በጀት አጠቃቀም 50% ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የልማት አጋሮች በጀት አፈፃፀም ዝቅተኛ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም በጀት የ2ኛ ዙር ገንዘብ ዘግይቶ ፈሰስ በመደረጉ ሲሆን በቀሪ ጊዚያት በጀቱን ለመጠቀም ጥረት ይደረጋል፡፡
23. የመ/ቤታችን የበጀት አጠቃቀምና የሐብት አስተዳደር በየጊዜው በውስጥ ኦዲተሮቻችን እየተፈተሸ ድጋፍ የሚደረግልን ሲሆን የ2007 ሒሳባችን ምክር ቤቱ በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ከመለስተኛ የአሰራር ግድፈቶች ውጭ ጉልህና መሰረታዊ ግኝቶች ባለመኖራቸው የኦዲት አስተያየቱ ***"ከዚህ በስተቀር"*** የሚል ነው፡፡

የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!

የተከበሩ ፕሬዚደንትየተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

መ/ቤታችን በ2007/2008 በጀት ዓመት ያከናወነውን የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

24. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው ሒሳባቸው በ2007/2008 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ የ249 መ/ቤቶች የ2007 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ነው፡፡ የ2006 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 70 (28.11%)፣ በዞን 9(3.62%)፣ በከተማ አስተዳደሮች 31 (12.45%) ቀሪዎች 139 (55.82%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡

25. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል:: የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው:: ከኦዲት ስልት አንፃር ከ249 መ/ቤቶች ውስጥ 206 (82.7%) በንሞና እንዲሁም 43 (17.3%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ ቀርቦባቸው በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

የኦዲት አስተያየት

26. የ2007 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 249 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 204 መ/ቤቶች ናቸው፡፡ 7(3.43%) መ/ቤቶች ***"ንፁህ የኦዲት አስተያየት"*** ፣ 192 (94.1%) መ/ቤቶች ***"ከዚህ በስተቀር"*** ፣ 5 (2.47%) መ/ቤቶች **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶአል፡፡ የኦዲት አስተያየቱ ከ2006 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር የከዚህ በስተቀር አስተያየት ተቀራራቢ ሲሆን ንፁህ የኦዲት አስተያየት በ6 መ/ቤቶች ጨመሮአል፣ አጥጋቢ አይደለም የኦዲት አስተያየት ደግሞ በአንፃሩ በ6 መ/ቤቶች ቀንሶአል፡፡ በሌላ በኩል የልዩ ኦዲት ጥያቄ ደግሞ በ9 መ/ቤቶች ጭማሪ አሳይቶአል፡፡ይህ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሚያሳየው የኦዲት ተደራጊዎች የፋይናንስና ሐብት አስተዳደር አንፃራዊ መሻሻል እያመጣ እንደሆነና የህዝቡ ብልሹ አሰራርን የመጠቆምና የመታገል ልምድ መነቃቃት እየታየበት የመጣ መሆኑን ነው፡፡

27. የ2007 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ነቀፌታ የሌለበት በመሆኑ **"ንፁህ የኦዲት አስተያየት"** የተሰጣቸው የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤ የደሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤ የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ የ2007 መደበኛና የULGDP ሒሳብ፤ የከተማ ልማት፤ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ የ2007 መደበኛና የULGDP ሒሳብ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና ስለ ሂሳቡ ትክክለኛ መሆን አለመሆን የሙያ አስተያየት ለመስጠት ባለመቻሉ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡- ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤ አዴት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤ አዴት ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፤ ደንበጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከልና ምስራቅ በላሳ ወ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡

የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ

28. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 5 (2.43%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሰረታዊ ለውጥ የታየበት ቢሆንም የመሻሻሉ ምክንያት ግን የክልሉ ገንዘብና ኢ/ት/ቢሮ ባደረገው ከፍተኛ ግፊት በመሆኑ ለወደፊቱ የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት በማያከብሩ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት ላይ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ብልጫ

29. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር *3,179,036.91* ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያዦች ብር *121,994.23* በጉድለት ተገኝቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ17 መ/ቤት ብር **9,434,520.85** **የሌጀር ከወጪ ቀሪ** በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ4 መ/ቤት በማነስ ብር 1,120,576.43 ተስተውሏል፡፡

30. ከጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ብር 21,305 የተመለሰ ብር 136,859 በፍታብሔርና በወንጀል ሂደት ያለ መሆኑ እና በተለይ በደብረ ማርቆስ ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በአጥፊዎች ላይ የእስራትና የገንዘብ ቅጣት የተወሰነባቸው ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን ይህ ሪፖርት

እስከተጠናከረበት 30/10/08 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች

31. 73 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት

ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ቆጢ

32. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 249 መ/ቤቶች ውስጥ በ69 መ/ቤቶች ብር **59,328,259.60** ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 50,487,477.56፣ ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ብር 3,348,511.80፣አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ብር 3,026,647.54 እና ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር 1156,930.08 ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ:: ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር 49,264.05(.08%) ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 59,278,995.55 የተሰበሰበ ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተጠናከረበት ሰኔ 30/2008 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልተሰጠበት ነው፡፡

ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ እና የሥራ ገቢ ግብር

33. በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር እንዲሁም ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሲከፈል መሰብሰብ የነበረበት የስራ ግብር ከ51 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 923,723.55 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ካሳሰብን በኋላ ብር 48,329.82 (5.23%) ብቻ እንደተሰበሰበ ከግብረ መልሱ መረዳት የተቻለ ሲሆን ቀሪው ብር 875,393.73 በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች

34. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሚልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ73 መ/ቤቶች ብር 27,435,531.20 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከፍተኛውን ከብር 200,000 በላይ የሚይዙት ጎንደር

ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 10,77,7031.65፤ የአዴት ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 9,212,289.14፤ ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,494,904.55 ፣ ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 673,843.05፣ ራያ ቆቦ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 660,040.00፣ ታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፊ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 656,138.34፣ ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 257,021.00፤፣ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 241,680.90፤ ሐብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 212,807.55 የያዙ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ስራ አልቀረቡም፡፡ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ደረሰኞቹ ቀርበው የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም ደረሰኙ ስለመቅረቡም ሆነ ስለመረጋገጡ በአጠቃላይም ስለተወሰደው እርምጃ በምላሹ አልተመላከተም፡፡

የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት

በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ

35. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ94 መ/ቤቶች ብር **828,281,282.42** በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሣብ

36. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች ብር 12,320,690.78 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቸ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ ይኸው ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች መካከል ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሠ/ማዕከል ብር 8,188,022.32፣ ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሠ/ማዕከል ብር 3,948,909.96፣ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ በመያዝ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

□ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት

የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች

37. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ11 መ/ቤቶች ብር 2**0,738,029.49** የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅመውበት ተገኝቷል፡፡ ከብር 200,000 በላይ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **በሰሜን ጐንደር ዞን ላይ አርማጭሆ ወረዳ የትክል ድንጋይ መሪ መዘጋጃ ቤት** ብር 2,500,000.00 ከሹማሪ-ገንብራ አዲስ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ለስራ ተቋራጭ ማህበር ቅድሚያ ክፍያ ሲከፈል የጨረታ ስርዓት ሳይሟላና በባዶ ቅጽ ላይ ውል በመያዝ አላግባብ የተከፈለ እና ስራው ሳይጀመር በመቅረቱ ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም የፍትህ አካላት በዚህ ጉዳይ ላይ ምላሽ ስላልሰጡ ጉዳዩ ያለበትን ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡
- **የአብክመ ገጠር መንገድ ባለስልጣን** ብር 702,843.33 የተለዩ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች ተከናውነው ለተቋራጮች በውሉ መሰረት ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳቀርብ የተፈፀመ፤ ብር 386,277.41 የኮንስትራክሽን ደርጅቱ በብድር ወስዶት ከነበረው ስሚንቶ እና ብረት ሂሳብ ውስጥ ሳይመለስ የቀረ ሂሳብ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት የተላከ ሲሆን በፍትህ ቢሮ በኩል ተጨማሪ ማስረጃ በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡
- **ደራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰማፅከል** ብር 469,998.42 ቀደም ሲል ስራው እንደተጠናቀቀ እና ሙሉ ክፍያው እንደተፈፀመ ለሚታወቅ የቢሮና አዳራሽ ግንባታ በውሉ መሰረት ለተቋራጩ ክፍያ ተፈጽሞ እያለ የቢሮው ግንባታ ስላላቀ በሚል ከመጀመሪያ የጨረታ ሰነድ የነበረውን የአማርኛ የስራ ዝርዝር ዋጋ ወደ እንግሊዘኛ በመቀየር በድጋሜ በውስን ጨረታ በማውጣት እና ከአሸናፊ ድርጅት ጋር ያለ ፍትህ ጽ/ቤት እውቅና ውል በመያዝ ለአንድ ግንባታ በድጋሜ የተፈፀመ ክፍያ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡
- **የደብረ ብርሃን እንጨት ማቀነባበሪያ ኃ/የተ/የግል/ማህበር** ብር 5,988,112.40 በድርጅቱ ግቢ ውስጥ የተገነባው የውስጥ ለውስጥ መንገድ እና የተለያዩ ግንባታዎች በተቋራጭ ሲከናወን ያለጨረታ፣ ህጋዊ ባልሆነ የግንባታ ስራ ውል እና ግዥውን እንዲያከናውን ህጋዊ ውክልና በሌለው ስራ አስኪያጅ በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ፤ ብር 270,384.72 የውስጥ ለውስጥና የተለያዩ ግንባታዎች ላከናወነው ተቋራጭ ከተፈፀመ ክፍያ ተሰልቶ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ብር 2,187,528.47 በድርጅቱ ግቢ ውስጥ የውስጥ ለውስጥ መንገድ እና የተለያዩ ግንባታዎች ላከናወነ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጸም የእንጨት ማቀነባበሪያ ድርጅት ስራ አስኪያጅ ህጋዊ ውክልና ሳይኖራቸው የተከፈለ እና መከፈል ከነበረበታ በላይ በብልጫ ተከፈለ፣ ብር 1,401,367.00 በድርጅቱ ተቀጥረው ከሚሰሩ ቻይናውያን ተሰብስቦ ለመንግስት ፈሰስ ያልተደረገ ከመቀጠር የሚገኝ የስራ ግብር፣ ብር

3,373,421.98 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጭ ፀድቀው የተገኙ የተለያዩ ዕቃዎች፣ ብር 609,218.31 ለተለያዩ አካላት ያለምንም ማስረጃ በወጭ ፀድቆ የተከፈለ ሂሳብ፣ ብር 866,840.73 ያለግባብ የተከፈለ የምግብና ምቹ ያልሆነ የስራ ቦታ አበል፣ በድጋሜ የተከፈለ የደመወዝ ክፍያ እና የተለያዩ እቃዎች ተገዝተው በብልጫ የተከፈለ ክፍያ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

- **የደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር** 204,273.00 ከንብረት ክፍል ወጭ ያልሆነን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ወጭ እንደሆነ በማስመሰል በንብረት ወጭ ደረሰኝ /ሞዴል 22/ ወጭ ከተደረገው ወረቀት ብዛት በኋላ ቁጥር በመጨመር በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም የዋለ፤ ብር 227,624.52 ተገዝቶ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሳይደረግ እና አየር በአየር ወጭ ተደርገው ለግል ጥቅም የዋሉ የተለያዩ ንብረቶች በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት 30/10/08 ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ

38. በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,758,527.25 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለዉ ደግሞ ታክሱ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመቆጣጠሪያ ስልት ስለማይኖረው ምን ጊዜም ሊሰበሰብ ስለማይችል አፈፃፀሙ የመግስትን ገንዘብ በማጭበርበር ከተጠቃሚው (ከከፋዩ) በመንግስት ስም ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል እንዲሁም በሌሎች ዜጎች ላይ ኢፍታዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር በደል የሚደርስ በመሆኑ ላለፈው ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በባለፈው ዓመት ሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ የለም፡፡

አላ□ባብ □ተ□ናመ □አ□

39. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ154 መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ

ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 13,917,929.12 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 200,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **ጤና ጥበቃ ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ** ብር 1,007,070.21 በሰሜን ወሎ ዞን ወልድያ ከተማ አስተዳደር እየተገነባ ላለው የእናቶችና ህፃናት ሆስፒታል 3ተኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፤
- **ግብርና ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ** ብር 752,961.31 የውሃ ጉድጓድ በአማራ ውሃ ቁፋሮ ድርጅት ሲያስቆፍር ከተያዘው ውል በላይ በብልጫ የተከፈለ፤
- **ትምህርት ቢሮ ብር** 409,588.62 የፕላዝማ ጥገና የተሰራበት፣የተለያዩ ግንባታዎች የተከናወኑበት በብልጫ የተከፈለ እና በመደበኛ ስራ ቦታቸው ለተገኙ ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የውሎና የስልጠና አበል፤
- **ጤና ጥበቃ ቢሮ** ብር 644,142.24 የተለያዩ ግንባታዎች ወጭ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ፤
- **አዴት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 511,752.77 አላግባብ የተከፈለ የኮብል እስቶን ጠረባ፣ምንጣፍ እና የማበረታቻ ክፍያ፤
- **ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 788,974.48 ከመመሪያ ውጭ አላግባብ የተደረገ ድጋፍ እና በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበልና ስልጠና አበል፤
- **አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 235,806.13 አላግባብ የተከፈለ ውሎ፣ስልጠና እና የበረሃ አበል፤
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 617,229.94 የአስተዳደሩ የቢሮ ግንባታ ከ1ኛ-3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከማስረጃ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የስልጠና አበል፤
- **ደጋ ዳሞት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 985,920.02 የአስተዳደር ቢሮ ግንባታ ሲከናወን ከውለታ በላይ ተከፍሎ የተገኘ፤
- **ነፋስ መውጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 261,098.95 ለዲች ቦይ ግንባታ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ፣ የመንገድ ስራ ሲከናወን ቅ/ክፍያ ሳይሰበሰብ የቀረ እና አላግባብ የተከፈለ የውሎና የስልጠና አበል፤
- **ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 692,130.00 የኮብል እስቶን ንጣፍ ሲከናወን ላልተሰራ ስራ የተከፈለ እና በድጋሚ ፀድቆ የተገኘ ወጭ፤

- **እንጅባራ ከተማ አስ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 369,942.18 በተለያዩ ሳይቶች ለተሰሩ የኮብል መንገዶች የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ግንባታ ከተሰራው ስራ በላይ የተከፈለ፤
- **ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 247,974.87 ግዥ ሲያከናውን ከተቀዳ ነዳጅ በላይ የተከፈለ ሂሳብ፣ ለ08 ቀበሌ መንገድ ግንባታ፣ለ04 ቀበሌ ወጣት ማዕከል፣ለጠባሴ መድሃኒያለም ትምህርት ቤት ሴፍቲታንከር ግንባታ የተለያዩ ዙሮች ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተፈፀመ፤
- **ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 208,851.00 የመንገድ ጠረጋ ሲያከናውን በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ እና አለአግባብ የተፈፀመ ውሎ አበል ክፍያ፤
- **ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 475,411.02 የፋብሪካ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም በብልጫ የተፈጸመ፣ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የቢሮ ግንባታ ሲከናወን እስከ መጨረሻ ዙር ያልተሰበሰበ ማቴሪያል ኦን ሳይት፤
- **ሳህላ ሰየምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ብር 383,274.17 ለተለያዩ መ/ቤቶች ግንባታ የቆርቆሮ ግዥ ሲያከናውን ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ፣ ነዳጅ ለማጓጓዝ ለመኪና ኪራይ የተጋነነ ዋጋ የተከፈለ፣ አላግባብ የተፈጸመ የደመወዝ፣ስልጠና እና የፈተና ምዘና ወጭ፣በባለሙያ አስፈላጊነቱ ሳይረጋገጥ የተገዛ የሞተር እና ዲፈረንሻል ግዥ እንዲሁም አለአግባብ የተፈጸመ ውሎ አበል፤

40. የ2007 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2006 በጀት ዓመት ብር 22,779,307.76 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ23 ሲቀንስ በገንዘብ መጠን ደግሞ uw` 8,861,378.64 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 762,049.81 (5.48%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ብር 13,155,879.31 ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ

41. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ44 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,059,727.70 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- ግብርና ቢሮ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማስፈፀሚያ ብር 5,612,018.63 በመራዊ ከተማ የቀዝቃዛ መጋዘን ግንባታ ሲከናወን ያለውል ስምምነት የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ፣
- ትምህርት ቢሮ ብር 5,329,562.99 የስፍር ልኬታ ሳይቀርብ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፣

- ፍኖተ-ሠላም ከተማ ነ/ፋ/ኢ/ል/ማ/ ብር 2,435,886.98 የኮብል እስቶን ንጣፍ እና አዲስ ጠጠር ንጣፍ ለማሰራት ውል የተያዘ ሲሆን ስራው ሳይጠናቀቅ እና ማስረጃው ሳይሟላ በወጭ የፀደቀ፣
- ታች ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 1,393,586.57 ለአስተዳደሩ የቢሮ ግንባታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ስራ ልኬት ሳይቀርብ የተከፈለ፣
- እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 1,012,965.89 ለመጣቶች መዝናኛ ማዕከል አዳራሽ ግንባታ ሲከናወን በባለሙያ ቅድመ የስራ እና የዋጋ ዝርዝር ሳይቀርብ እና የዕጅ ጉድጓድ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ጊዜያዊ ርክክብ ሳይደረግ የተፈጸመ ክፍያ፣
- ወልድያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 13,420,024.50 የግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከመፈፀሙ በፊት የስራ ዝርዝር፣ የስራ ልኬት ማስረጃ ሳይቀርብ እና በመሃንዲስ የተረጋገጠ የክፍያ የምስክር ወረቀት ሳይዘጋጅ የተፈጸመ ክፍያ፣
- ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 1,455,787.27 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲገነባ በተቋራጩ የስራ ልኬት ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣
- ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 2,384,550.85 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣
- ከምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 1,354,358.59 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣
- ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ኢ/ል/ማዕከል ብር 4,852,063.00 የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲያከናውን የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ናቸው፡፡

42. ከዚህ በላይ በተገለፁ መ/ቤቶች ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ

43. ማንኛውም □አ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለፍ በ87 መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር **24,831,883.94** የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና ተመ□□ቦ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 24,409,008.63 ጋር

ሲነፃፀር በ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ9 ቀንሶ እና በገንዘብ መጠን ብር 422,875.31 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ያለው ችግር በተመሳሳይ ሁኔታ መሄዱን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ችግር ቀላል ሥላልሆነ በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚያመለክት ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች

44. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ34 መ/ቤቶች ብር 55,072,281.07 የተገኘ ሲሆን ከብር 200,000 ብር በላይ ከያዙ ከመ/ቤቶች መካከልም፡- ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 588,422.62፣ ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 321,035.81፣ ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 248,144.57፣ አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 546,137.53፣ ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,474,009.80፣ ጣቁሳ ወወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,967,664.25፣ አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 3,165,514.58፣ ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 303,229.33፣ ጀናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 919,612.50፣ ሊቦከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 244,821.68፣ ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,804,578.82፣ ለገሂዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 233,164.57፣ ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ ሰ/ማዕከል ብር 3,861,927.65፣ ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,353,673.81፣ ወልድያ ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,413,365.26፣ ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ /ሰ/ማዕከል ብር 5,281,091.12፣ ኤፍራታ ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,110,096.35፣ ሸዋሮቢት ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 687,968.37፣ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 214,848.67፣ መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 336,678.65፣ ባቲ ከተማ አስ/ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,283,499.51፣ አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 500,871.14፣ ጁሌጥሙጋ ብር 547,107.00 ይገኙበታል፡፡

45. ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ

46. □ቃቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ□ □ቃቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች □ተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ166 መ/ቤቶች ብር 126,923,643.06 ዥ□ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ የግዥ አፈጻፀም ጉድለት ጎልቶ የታየባቸውና ከብር 1,600,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- ደቡብ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 15,764,772.60 ለመምሪያው ሴክተር መ/ቤት ህንፃ ግንባታ ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣ አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,606,923.31 የሻውራ ወረዳ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የአጥር ግንባታ እና የተለያዩ እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ እና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ካላቀረበ አቅራቢ የተፈፀመ፣ ጃቢጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,809,311.97 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ፣ የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ እና በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ወቅት ከፍተኛ ግዥ የተፈፀመ፣ሜጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,961,388.20 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ እና የፖስታው የመክፈቻ ቀን ሳይደርስ ከመመሪያው ውጭ በመክፈት የተከናወነ፣አዊ ብሔረሰብ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,202,098.09 የውሃ ተቋማት ግንባታ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 3,186,981.22 ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ እና የግዥ ጥያቄ/የስራ ትዕዛዝ/ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,584,342.98 ግዥ ሲፈጸም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣ በረኸት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 6,414,531.20 የተለያዩ ዕቃዎች እና የዶዘር ኪራይ ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣ አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,759,161.67 ግዥ ሲፈፅም አሳማኝ ምክንያት ሳቀርብ በቀጥታ፣ በፕሮፎርማ እና በውስን ጨረታ የተፈፀመ፣ ለጋንቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,875,147.88 ግዥ ሲፈፅም ያል ግልጽ ጨረታ እና ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣ ከለላ ወረዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,832,472.97 ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ፣ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ፣በውስን ጨረታ፣በቀጥታ ግዥ እና የተገዛው ዕቃ የንብረት ደረሰኝ ሳቀርብለት መገኘቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የዕቃ ግዥ መመሪያ በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ

እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

47. የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግኝ ሂሳብ ከ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 95,503,044.41 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ53 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን በብር 31,420,598.96 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግኝ መመሪያውን ተከትሎ በመፈጸም በኩል መሰረታዊ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት

48. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መካከል በ106 መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!

የተከበሩ ፕሬዚደንት!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

ማጠቃለያ

የ2008 በጀት ዓመት የ11 ወር ዕቅድ አፈፃፀምን በሚመለከት

49. በ2008 በጀት አመት በኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ የተደረገ መሆኑና በቀጣይ ጊዜያት ሙሉ የሰራዊት አቅም ላይ የደረሰ ፈፃሚ ሃይል እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከኦዲት ሽፋን አንፃር በመ/ቤት ቁጥር ከ58 በመቶ በላይና በበጀት ከ78 በመቶ በላይ አፈፃፀም መኖሩ አበረታች ነው፡፡ በክዋኔ ኦዲት ረገድ የበጀት ዓመቱ አፈፃፀም በአማካይ ከ 95 በመቶ በላይ ቢሆንም በአጠቃላይ ሽፋን ግን በሰፊው መስራት ይኖርብናል፡፡

የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት

50. የ2007 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ከተደረጉ 204 መ/ቤቶች ውስጥ ከ94 በመቶ በላይ የሚሆኑት **"ከዚህ በስተቀር"** የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙ በመሆኑ አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መሰረት አድረገው በጀትን ለመምራት የተሻለ ዝግጁነት ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል ንፁህ የኦዲት አስተያየት የሚሰጣቸው መ/ቤቶች ቁጥር መጠነኛ መሻሻል ማሳየቱና አስተያየት መስጠት አልተቻለም የሚል የኦዲት አስተያየት ያላቸው መ/ቤቶች ውስን መሆኑ በበጎ የሚታይ ነው፡፡

ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት

51. የ2007 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በምላሽ አሰጣጥ ረገድ ግፊት ያለበት ቢሆንም መሰረታዊ መሻሻል የታየበት ነው፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት

52. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,179,036.91 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያገኙ ብር 121,994.23 በጉድለት ተገኝቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ17 መ/ቤት ብር **9,434,520.85 የሌጀር ከወጪ ቀሪ** በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ4 መ/ቤት በማነስ ብር 1,120,576.43 ተስተውሏል፡፡ 73 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ

30/2007 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

የገቢ ሂሣብን በተመለከተ

53. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 249 መ/ቤቶች ውስጥ በ69 መ/ቤቶች ብር 59,328,259.60 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ73 (35.43%) መ/ቤቶች ብር 27,435,531.20 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት

54. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ94 መ/ቤቶች ብር 828,281,282.42 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ የ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች ብር 12,320,690.78 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቸ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ67 መ/ቤቶች ብር 537,949,080.04 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የወጪ ሂሳብን በሚመለከት

55. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ11 መ/ቤቶች ብር 20,738,029.49 የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅመውበት ተገኝቷል፡፡ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ154 (74.75%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 13917929.12 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ44 (21.35%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 45,059,727.70 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

56. ማንኛውም □አ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተቁ□ ማስረጃ መቅረቡ መረ□ቶዓ ሲቁ ይህን በመተላለፍ በ87 (42.23%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር

24,831,883.94 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና ተመ□□ቦ ተገኝቷል:: ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ34(6%) መ/ቤቶች ብር 55,072,281.07 ተገኝቷል፡፡ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ166(80.58%) መ/ቤቶች ብር 126,923,643.06 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት

57. የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ49 መ/ቤቶች ብር 64,188,419.24 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ

58. በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 206 መ/ቤቶች መካከል በ106 (51.46%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!

የተከበሩ ፕሬዚደንት!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፣ በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግና የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያቶች አቀርባለሁ፡፡

59. **የኦዲት ሽፋንን ሊያሳድጉ የሚችሉ የኦዲት ተደራጊዎች አደረጃጀትና ሒሳብ ተጠቃሎ የሚያዝበት አሰራር ሊፈተሽና ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል፡፡**

ይህ የማሻሻያ ሃሳብ በዚህ ምክር ቤት በተደጋጋሚ የተነሳና አቅጣጫ የተቀመጠበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በመሆኑ፡-

- በጀታቸውን ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚይዝላቸው በየዓመቱ ቁጥራቸው እያደገ የመጣው የጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችን የሂሣብ እንቅስቃሴ አማክሎ የሚከታተል በየወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በፑል ተደራጅተው የጋራ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚይዝላቸው የአካል ተሃድሶ ማዕከላት የሂሳብ ሪፖርት ለቢሮው ሲያቀርቡ የሂሣብ ማስረጃዎችንም የሚያስረክቡበት ሁኔታ ቢመቻች፣-
- በጀታቸውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚይዝላቸው በዞንና በወረዳ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሂሣብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ስራቸው ላይ ተጽዕኖ በማያመጣ መልኩ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል በኩል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የሚይዝላቸው ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

60. **የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡**

የኦዲት አገልግሎቱ በየዓመቱና በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑ ምክንያት ኦዲት ተደራጊ ተቋማት ከኦዲቱ ትምህርት እያገኙ፣ በግኝቶች ላይም አስተማሪና አጥጋቢ እርምጃ እየወሰዱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸው የተጠናከረና የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትም በዛው ልክ እየገለበተ ሊሄድ ይገባል፡፡ ሆኖም፣ ተደጋጋሚ ግኝቶች የሚስተዋሉበት ሁኔታ መሰረታዊ

መሻሻል ያላመጣ በመሆኑና ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በግብረ-መልስነት ተወስዶ ሲታይ በአብዛኛው ሒደትን የማሳየት አዝማሚያ ያለው በመሆኑ ኦዲት ተደራጊዎች በኦዲት አገልግሎቱ አጠቃላይ መሻሻል እንዲያደርጉ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

61. **በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ይገባል፡፡**

ከግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

62. **የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት መዝጋት ያስፈልጋል፡፡**

በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

63. **የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ነው፡፡**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

64. **በየደረጃው ያሉ የህዝብ ም/ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ጠንካራ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡**

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጪ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል፡፡

65. በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በዚህ ምክር ቤት ሲቀርብ የነበረውን የኦዲተሮች የተለያዩ ጥቅማጥቅም ጥያቄዎች አሁን በደረስንበት ነባራዊ ሁኔታና ቀጣይ የሚተገበሩ

አሰራሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መንግስት ለጥያቄው ምላሽ የሰጠ በመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ በመ/ቤቱና በኦዲተሮች ስም ማመስገን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳያችሁት ታታሪነትና መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ደሴ ጥላሁን አያሌው

ዋና ኦዲተር

ሐምሌ 2008 ዓ.ም

ባህር ዳር!!